ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥር 22 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ምን ይዞ ጉዞ?

በሶ ተይዟል? ቂጣ አለ ዱቄት? ወይስ በዘመኑ ይሁንና የመጉዳኘ ቲኬት ተቆርጧል፤መግዣው ገንዘብ አለ ? በርግጥ ጉዞ ው ራሱ ግብ ነው መዳረሻ ነው ብለው ሚያምኑም አሉ ። የትግል ጉዞ ከጀመርን ዓመታት አልፈዋል ። ወያኔን እንኳን ቢያንስ ለ28 ዓመት ታግለነዋል ። በአጼውና በደርግ ጊዜ ያደረግነውን ስንጨምርማ አይጣል ነው ። ታዲያ እኛ 40 ዓመት በላይ የታገልነው ሳንፈታ፤እነሱ ያውም ሳይታገሉና ከነበረው አገዛዝ ጋር ሰምረው ሲቧርቁ የነበርሩት ምነዋ ትግል አስመረራቸው ብለን መጠየቅ ተገደናል ። ከመቸውም እንዲህ ጸረ ወያኔ እንደሆኑም ገርሞናል ። አህያ ያየ የጅብ መንጋ ይመስል ሀገርን ሊቀራመቱ ተጠራርተው መምጣቸውንም አይተናል ። መድረኩ ተከፍቶላቸው የትላንት ጸረ ሕዝቦች የዛሬ የክብር እንግዳ ተብለው ኢትዮጵያን ለቅርጫ አቅርበው ሊቦጫጭቋት አሰፍሰፈዋል ። ትግሉ ከግብ ሳይደርስ እንዲቆምም ለወያኔ ስርዓት ወጌሻ የሚሆኑ በባዕዳን ተሹመውልናል ። በዚህ ሁኔታ የምን ትግል በቃ? ምን ይዞስ ነው ጉዞ ?
የምንጠይቃቸው ወይም መፈክሮቻችን ቢደጋገሙ ወይም ሲተቹን እንደሚሉት ያው ቢሆኑ ምክንያቱ ሁኔታው አልለወጥ በማለቱ ብቻ ነው ። በየካቲት 66 ያነሳናቸው መፈክሮች የዛሬ ሆነው የሚገኙት ምላሽ አጥተው በመቀጠላቸው ነው ። በየካቲት 66 ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስትን ጠየቅን--ምላሹ ወታደራዊ አገዛዝ ሆነ ። የሽግግርን ሂደት ወሳኝና ማናልባትም ብቸኛ መፍትሔ ነውና ይኸው እስከዛሬ የሽግግር ሂደትና የሽግግር መንግሥት ጥያቄያችን ወቅታዊ ሆኖ ይገኛል ።ዴሞክራሲ መብት ለሕዝብ፤የሀገር ሉዓላዊነት፤ ነጻነት፤እኩልነት፤የፖለቲካ እስረኞች መፈታት፤ፍትሃዊ አስተዳደር፤ የሴቶች መብት መከበር፤ድህነትና ስራ አጥነትን ማስወገድ ወይም መቅረፍ መቀነስ፤ የሀገር አንድነትን ማስከበር ወዘተ--በሁሉም መስክ ችግሮቹ ቀጠሉ እንጂ ያገኙት መፍትሔ የለም ። ሹሙ በአማካሪዎቹ አማካይነት አስመሳይ የለውጥ እርምጃዎችን የወሰደ ቢመስልም በመሰረቱ ግን ቢከፍቱት ተልባ ሆኖ ይወገድ ያልነውን የገማ አገዛዝ እያስቀጠለብን ነው ። በግል ጥቅም ያልታወረ፤ለከርሱ ያላደረና እንዲያው በደፈናው መሃይም ያልሆነ የዚህን ሀቅነት ሊክድ አይችልም ። ወደ ምርጫ እንጓዛለን ሲሉ ምን ይዞ ጉዞም የምንላቸው የነጻ ምርጫ ሁኔታ መቸም በኢሕ አዴግ ስር ሊሟላ እንደማይችል ከተመክሮ አይተን ያወቅነው በመሆኑ ነው ። ሹሙ ሁሉን መቀመጫ ኢሕዴግ አሸነፈ ብሎ ባዕድ ድጋፊዎቹን የሚያሳፍር ባይሆንም ነጻ ምርጫ በወያኔ ኢሕ አዴግ ስር ሱሚ ስለመሆኑ መተንበዩ ነቢይ አያሰኘንም ። ሆኗል፤አይተነዋል፤ደምም ገብረን በጉልበት አረመኔውና ዘረኛው ስርዓት ቆይቶብናል ። በ 2020 የሚመጣ ምንም ዴሞክራሲያዊ ተዓምር አይኖርም ። እርምን ከወዲሁ ማውጣት ይበጃል እንላለን ። በመሆኑን ምርጫ ምርጫ ብከው ሹሞቹን የደገፉ ሁሉ --ያውም ባለው ሁኔታ--ለኢትዮጵይና ለሕዝቧ ጥቅም የቅሙ ናቸው ማለት ያዳግታል ።አሜሪካ በሚወስንላቸው መሰረት የተወሰነ በርጩማ ሊያገኙ ቢችሉም ለሕዝብ የሚፈይደው የለም ። ያው ያው ሁሌም ያው፤በዘረኞች መገዛት መጋዝ መነዳት መፈጀት።
ምን ይዞ ጉዞ ስንላቸው ጊዜ ስጡት ለሚሉን መልሱ የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃልን ነው ። ለነገሩ ሕዝብ የጠላውን ስር ዓት ለማስቀጠል መጣር፤ሕዝብ ያወገዛቸውን ወነጀለኞች በላዩ ላይ መሾም፤ ለዘረኞች መመቸት ለውጥ ማምጣት ሳይሆን ትግልን ማፈንና አብዮት ሊሆን ይችል የነበረውን ትግል መቀልበስ ነው ። የእኛው ቀርቶ የግብጽና የአረብ

ህገሮች ትግሎችን ማጤኑ ይበቃል ። ባለነፍጥ በሌላ ባለነፍጥ በተተካ ቁጥር፤አስጠንቃቂና መካሪ ባልጠፋበት ሁሌም መታለልና ስብዕናን ማስደፈር ያስገምታል ። ፋሺስቱን ኮለኔል ያኔ ቀርቶ ዛሬም የሚያወድሱ እንዳሉ መዘንጋት የለብንም ። የመለስንም ጭፍሮችና አዳናቂዎች የወገኖችን ገዳይ አውሬ ሲያመልኩ ታዝበናል። ለሹሙ እየተካሄደ ያለው ጣኦት ጠረባ ደግሞ አሳፋሪ ደረጃ ደርሶ እንደነበር ሁላችንም አይተናል፤ታዝበናል ። ሰውን ከአምላክ ማመሳሰል በሃይማኖቶችም ቢሆን የሚፈቀድ አይደለም ። ከመነሻው ጥያቄው ታግለን ደምተን ከግባችን ደረስን አልደረስንም የሚለው ነው ። ጊዜ ሰጥቶ ለመጠበቅማ የደላው ሙቁን እያኘከ መከረም መዘፍዘፍም ይችላል ። ሀግርና ሕዝብ ሲደሙ እያየን ግን ፍቅር ወሰላም ሰበካ ባይጥመን ሊፈረድብን አይገባም ። ለተራበው፤ለመንግገድ አዳሪው፤በጉድጓድ እስር ቤት ለሚማቅቀውማ ውያኔ ኢሕ አዴግ በ28 ዓመት አይደለም በ28 ቀኑ መውደቅ መወገድ የነበረበት ነው ። እናቱ ገበያ የሄደችበትና እናቱ የሞተችበት ቢያለቅሱም ለቅሶአቸው አንድ አይደለም።ሰምሃልና የኔው ብጤ ልጅ እኩል አይደሉም፤እኩል አልተጎዱም፤እኩልም አልደላቸው ። ችግር አንጻራዊ ነው ካልተባለ በቀር ። የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ስንል ጥቂቶች ተፈተው ብዙዎቹ በዚያው በጉድጓዶቹ ይከረሙ በሚልም አይደለም ። ዴሞክራሲ ስንል ፍፁም ሙብትን መቸም ላልመረጥነው ሹም ሰጥተን የበዪ ተመልካች እንሁን በሚልም አልነበረም ። በዕርቅና ሰላም ሽፋንም ሀገራችንን ለአረቦችና ለሻዕቢያ አሳልፈን እንስጥ ማለታችንም አልነበረም ። ሉአላዊነት ስንልም ሀገራችንን የባዕድ ሎሌ መጫወቻ ማድረግ ማለታችን አልነበረም ።ከሁሉም በላይ ግን የሽግግር ሂደት ስንልና ስንሰዋም ወያኔ በፍራሽ አሳዳሽ ተክቶና ጠግኖ ኢሕ አዴግ በሚል ማስቀጠል ማለታችን አልነበረም ።የትግላችን አልፋም አሜጋም የጠላነውን ስርዓት አስወግደን ሕዝባዊ ዴምክራሲያዊ መንግሥትና የኢትዮጵያ አንድነት እውን እንዲሆኑ ለማድረግ ሀገራችንን ለጽንፈኛ ዘረኞችና ገንጣዮች ለንሰጥ አልነበረም ። የሹሙ ይዘት በተያያዘው ሂደት ይገለጣል ። ዛሬ ኢትዮጵያ በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ ከሰጠን ምንም መደናገር አይኖርም ።

ምን ይዞ ጉዞ ስንል ለመሰረታዊ ለውጥ ምን ድላዳልስ አለ ማለታችንም ነው ። እየተወሰደ ያለው እርምጃ በአብዛኛው--ልፈፋና ድለላውን ትተን--ለለውጥ አስተማማኝ መሰረት እየጣለ አይደለም ። በምርጫው ሂደት ጥያቄ የተነሳበትን በዋና መልኩ--ህጉ ጠብቆ በራስ ውሳኔ የምርጫ ቦርድ ሀላፊ ብሎ መሾሙ ራሱ አጠያያቂ ነው ። ቢያጎበድድለትም ህብረ ብሔር ድርጅቶን ገለል አድርጎ ጠባቦቹን አቅፏል ።ከሻዕቢያ ጋር ዕርቁ አሜሪካ፤ ሳውዲና ኤሚሬትስና ያስደስት ይሆን እንጂ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ አይደለም በተለይ በተደረገበት የመሬት ቆርሶ መስጠት መንገድ ። ሱዳን መሬታችንን እንደያዘ ነው ። ወያኔም ከጎንደር ወሎ አፋር የሰረቀውን መሬት ሊመልስ ቀርቶ መተማም የእኔ ነው እስከማለት ደርሶ ይገኛል ። አውሬ ወያኔዎች የልብ ልብ እየተሰማቸው ነው ። የትግራይን ሕዝብ ከወያኔ ለመነጠል ሊደረግ የሚገባው ስልታዊ ቅስቀሳ እየተደመጠም አይደለም ።በወያኔ ኢሕ አዴግ ሠራዊትም ውስጥ ወደ ሕዝብ ፊታቸውን እንዲመልሱ-በወያኔ ኢሕአዲግ ላይ እንዲያምጹ በቂ ቅስቀሳ ገና ጊዜውን እየጠበቀ ነው የሚያሰኝ ሆኖ ይገኛል ። ምን ይዞ ጉዞ?ጉዞስ ወደየት ? ያለነበትን ሁኔታ መመርመርና ትክክለኛ ግንዛቤን ይዞ ትግልን መቀየስ የግድ ነው ። ትግላችን ሀገራችንን ኢትዮጵያ ከጥፋት ለማዳን ነውና በቸልተኝነት ሆነ በጥቅም በመገዛት ግዴትታችንን ልንዘነጋ ማንም ሆነ ማንም አይፈቅድልንም ። አንድነታችንን አጠናክረን ይዘነው፤ተያይዘነው የነበረውን ትግል አፋፍመን መቀጠል አለብን ።

ጸረ ወያኔ ኢሕ አዴግ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !!

ኢትዮጵያዊነት አቸናፊ ነው !!